መልእክት ስድስት

## ለሕይወት አገልግሎት የሕይወት ዛፍ የሆነው
## የክርስቶስ ርቢ መሆን

የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ፡- ዮሐ. 1፡4፤ 12፡24፤ 15፡1፣4-5፤ 1 ዮሐ. 5፡16፤ 2 ቆሮ. 4፡12

**I. በእግዚአብሔር ኢኮኖሚ ውስጥ የሕይወት ዛፍ ተመጋቢዎች ብቻ ሳንሆን የዚህ ዛፍ ቅርንጫፎች ጭምር ነን፣ በስተመጨረሻም እንደ ሕይወት ዛፍ የክርስቶስ ርቢ፣ ትንሽ የሕይወት ዛፍ መሆን እንችላለን—1 ጴጥ. 2፡21፤ ዮሐ. 1፡4፤ 12፡24፤ 15፡1፣4-5፡-**

ሀ. የእግዚአብሔር ውጥን በክርስቶስ ያመኑት ሁሉ አምላክ-ሰው የሆነው የክርስቶስ ርቢ ይሆኑ ዘንድ ነው—12፡24፤ ሮሜ 8፡29፡-

1. የክርስቶስ ርቢ መሆን እስትንፋሳዊ ከሆነው ክርስቶስ በመንፈሳችን ዳግም መወለዳችንን፣ ከዚያ ደግሞ በእስትንፋሳዊው ክርስቶስ ቀስ በቀስ በነፍሳችን መለወጣችንን ይጠይቃል—ዮሐ. 3፡6፤ 2 ቆሮ. 3፡18።
2. የክርስቶስ ርቢ የምንሆነው የመለኮታዊው ሕይወት ብልጥግናዎች ወደ ውስጣችን መታደላቸውን እና እኛ እነርሱን መለማመዳችንን በሚያካትተው ሂደት ነው—ኤፌ. 3፡8፤ ቆላ. 3፡4፤ 10-11።
3. ሞዴላችን የሆነው የክርስቶስ ርቢ ለመሆን ክርስቶስን በውስጣችን እንደሚኖር ማንነት፣ በእኛ ውስጥ እየተሠራ እንዳለው ማንነት እና በልባችን ቤቱን እየሠራ እንዳለው ማንነት መለማመድ ያስፈልገናል—ገላ. 2፡20፤ 4፡19፤ ኤፌ. 3፡16-17።
4. የክርስቶስ ርቢ ስንሆን በተትረፈረፈው የመንፈሱ አቅርቦት ቅጽበታዊ በሆነ መልኩ ክርስቶስን እንኖራለን—ፊልጵ. 1፡19፣ 21።

ለ. በዘፍጥረት 2፡9 የሕይወት ዛፍ ልዩና ብቸኛ ነበር፣ ነገር ግን የሕይወት ዛፍ እኛ ውስጥ ተተክሏል፣ ትንሽ የሕይወት ዛፍ እንድንሆን በማድረግ በውስጣችን እያደገም ነው።

**II. የሕይወት ዛፍ እንደሆነው እንደ የክርስቶስ ርቢ፣ የሕይወት አገልግሎት አለን—1 ዮሐ. 5፡16፤ 2 ቆሮ. 4፡12፡-**

ሀ. በክርስቶስ ያመንን እና የእግዚአብሔር ልጆች ስለሆንን የዘላለም ሕይወት ያለንና የዘላለምን ሕይወት የምንለማመድ ብቻ ሳንሆን፣ ወደ ሌሎች የክርስቶስ አካል ብልቶች ይህንን ሕይወት ማገልገልም እንችላለን—1 ዮሐ. 5፡11-16።

ለ. ሕይወትን ማገልገል ሕይወትን ማካፈል ነው፤ የሕይወት መትረፍረፍ ሲኖረን ከዚህ አቅርቦት ሌሎችን ማገልገል እንችላለን—1፡1-2፤ 2፡25፤ 5፡11-13፣ 16።

ሐ. በቤተ ክርስቲያን ያለው አገልግሎት ሕይወት-የማገልገል አገልግሎት—ለሌሎች መለኮታዊውን ሕይወት የማቅረብ አገልግሎት—ነው—2 ቆሮ. 4፡12፡-

1. በዚህ ነጥብ መደመም እና አገልግሎታችን የሕይወቱ መውጫ ይሆን ዘንድ የጌታን ፊት መፈለግ ያስፈልገናል—ዮሐ. 11፡25፤ 1 ዮሐ. 1፡2።
2. ለሌሎች የምናቀርበው ሕይወት በመንፈስ ነው፣ መንፈስ ከመንፈሳችን ጋር ተዋሕዷል፣ የእግዚአብሔር ሕይወትም በተዋሐደው መንፈስ ውስጥ ይገኛል፣ ይኖራል፣ ያድጋልም—1 ቆሮ. 15፡45፤ 6፡17፤ ሮሜ 8፡4፡-
   ሀ. ለቅዱሳን የሕይወትን አቅርቦት ለመስጠት ከፈለግን፣ መለኮታዊው ሕይወት በተዋሐደው መንፈሳችን ውስጥ ስለሆነ መንፈሳችንን መልቀቅ አለብን—7፡6፤ 1፡9።
   ለ. መንፈሳችን መለቀቅ ካልቻለ መለኮታዊው ሕይወት የሚለቀቅበት ምንም አይነት መንገድ የለም—8፡10።

መ. እንደ ሕይወት ዛፍ እንደ የክርስቶስ ርቢ ለመኖር ሕይወትን ማገልገል መቻል አስፈላጊ መሆኑን በተመለከተ በጥልቀት መደመም ያስፈልገናል—1 ዮሐ. 5፡11-16፡-

1. እግዚአብሔር ከእኛ የሚፈልገው አገልግሎት ሥራን በመሥራት ላይ ሳይሆን ሕይወትን በማገልገል ላይ ያተኩራል—ቁ. 16።
2. ለሌሎች ሕይወትን ለማገልገል ከክርስቶስ ጋር መጋጠም፣ በክርስቶስ ውስጥ መኖር እና ሕይወቱ፣ ባሕሪው፣ ፍላጎቱ እና ዝንባሌው ሕይወታችን፣ ባሕሪያችን፣ ፍላጎታችን እና ዝንባሌያችን ይሆኑ ዘንድ እንዲሞላን ለእርሱ ስፍራን መስጠት ያስፈልገናል—2፡27፤ ኤፌ. 3፡16-17።

ሠ. ሕይወትን ማገልገል የሕይወት ሞልቶ መፍሰስ ያለው ሰው መሆን ነው፤ አገልግሎታችን ሌሎችን በመለኮታዊው ሕይወት አቅርቦት ለመሙላት የእግዚአብሔር ከእኛ ውስጥ መፍሰስ ነው—ዮሐ. 19፡34፤ 7፡37-39፡-

1. ሕይወት የእግዚአብሔር ይዘት እና የእግዚአብሔር መፍሰስ ነው፤ የእግዚአብሔር ይዘት የእግዚአብሔር ማንነት ሲሆን፣ የእግዚአብሔር መፍሰስ የእርሱ እንደ ሕይወት ለእኛ መካፈል ነው—ኤፌ. 4፡18፤ ራእ. 22፡1።
2. ሕይወት ከመንፈሳችን ይለቀቅ ዘንድ፣ የውጪው ሰዋችን መነካት እና መሰበር አለበት—2 ቆሮ. 4፡16፤ ዕብ. 4፡12፦
   ሀ. የውጪው ሰዋችን ካልተሰበረ የመለኮታዊው ሕይወት ንጹህ ፍሰት ሊኖር አይችልም—ዮሐ. 7፡38።
   ለ. መለኮታዊው ሕይወት ከውስጣችን እንዲለቀቅ ከፈለግን፣ ነፍሳችን መገዛት አለባት፣ መንፈሳችንም እያንዳንዱን ጉዳይ እንዲቆጣጠር እና እንዲገዛ መፍቀድ አለብን፤ ያኔ የጌታ ሕይወት መፍሰስ ይችላል—ኤፌ. 3፡16-17።
3. የሕይወት ሞልቶ መፍሰስ ያለው መሆን ሕይወትን በሚለቀው ሞቱ ከክርስቶስ ጋር ጋር አንድ መሆናችንን ይጠይቃል፤ ይህ በተመታው ዓለት ከተመሰለው ክርስቶስ ጋር አንድ መሆን ነው—ዮሐ. 19፡34፤ ዘጸ. 17፡6፦
   ሀ. የተመታው ዓለት ከሆነው ከክርስቶስ ጋር አንድ ስንሆን መለኮታዊው ሕይወት እንደ ሕያው ውኃ ከእኛ ይፈሳል—ቁ. 6፤ ዮሐ. 7፡38።
   ለ. ሕያው የሆነው ውኃ ከውስጣችን ይፈስ ዘንድ የሰብዕና ሕይወታችን፣ ተፈጥሮአዊው ሕይወታችን መመታት አለበት—2 ቆሮ. 4፡10-11፣ 16።
   ሐ. ከተመታው ክርስቶስ ጋር አንድ ከሆንን የተፈጥሮአዊውን ሕይወታችንን መሰቀል እንለማመዳለን፣ ከዚያም በሰብዕና ሕይወቱ መመታት የክርስቶስ መለኮታዊ ሕይወት እንደ ሕያው ውኃ እንደፈሰሰ እንዲሁ እኛም በተፈጥሮአዊው ሕይወታችን መመታት የሕይወት ውኃውን ፍሰት እንለማመዳለን—10-12።

ረ. ለሌሎች ሕይወት ማገልገል ከፈለግን በቤተ ክርስቲያን ላይ በሞት፣ በገሃነም ደጆች የሚመጣውን ጥቃት ማወቅ ያስፈልገናል—ማቴ. 16፡18፤ ሮሜ. 5፡17፦
1. ከእግዚአብሔር የሆነው ነገር በሕይወት፣ ከሰይጣን የሆነው ነገር በሞት ይገለጻል፤ በቤተ ክርስቲያን ከእግዚአብሔር የሚወጣው ነገር ሁሉ ሕይወት ነው፣ ከሰይጣን የሚወጣው ነገር ሁሉ ሞት ነው—ዮሐ. 11፡25፤ ዕብ. 2፡14።
2. ቤተ ክርስቲያንን በተመለከተ የሰይጣን ታላቅ ፍርሃት ለሞት ኃይል ያላትን ተቃውሞ ነው—2 ጢሞ. 1፡10።
3. በውስጣችን ያለው ዘላለማዊው ሕይወት በእኛ ውስጥ እና በሌሎች የቤተ ክርስቲያን ብልቶች ውስጥ ያለውን ሞት ድል መንሣት ይችላል—1 ዮሐ. 5፡11-13፣ 16።
4. የሕይወት ዛፍ እንደሆነው እንደ የክርስቶስ ርቢ፣ የዘላለምን ሕይወት መለማመድ እና የዘላለም ሕይወት ሊፈስበት የሚችል ማስተላለፊያ በመሆን ለሌሎች ይህን ሕይወትን ማገልገል ያስፈልገናል—ዮሐ. 7፡37-39፤ ፊልጵ. 1፡24-25።

*© 2022 Living Stream Ministry*